Food and Agriculture Organization of the United Nations

UNDP — Empowered lives. Resilient nations.

UN environment

UN-REDD PROGRAMME

CIFOR



# ዘላቂ የደን አስተዳደር በኢትዮጵያ ቆላማ ስፍራዎች

2011 (E.C.)

ስተበኒያቲ አትማጃ፣ አበጀ እሸቴ እና ማኑኤል ቧሲየር

**እ.ኤ.አ 2013 በኢትዮጵያ ከሚገኘው የደን ኃብት 80 ከመቶ የሚሆነው የዝቅተኛ ስፍራ ወይም የቆላ ደን ነበር፡፡** የኢትዮጵያ አጠቃላይ የደን ኃብት ስነ-ምሕዳር (ይህን የደን ኃብት ጨምሮ) «አፈሮሞንታና» የሚባለውን በማዕከላዊው የአገሪቱ ከፍተኛ ቦታዎች ያለውን የደጋ ደንና የቦረና ሞቃታማ አካባቢ እንጨታማ ደንን (woodlands) ያጠቃልላል፡፡ አብዛኛዎቹ ብርቅዬ የአገሪቱ የዱር አራዊትና አዕዋፍት በዚህ ደረቃማ አካባቢ ደን የሚገኙ ሲሆነ ደኑ የአካባቢውን ስነ-ምሕዳር ሚዛን በመጠበቅ ረገድ የራሱን ከፍተኛ ድርሻ ያበረክታል፡፡

**ባለፉት ሁለት ዓስርተ-ዓመታት የቆላ ደን ለእርሻና መኖሪያነት ለመሳሰሉ አገልግሎቶች በመቀየሩ በፈጣን ሁኔታ በመራቆት ላይ ይገኛል፡፡** በደጋው አካባቢ የሚታየው የእርሻ መሬት እጥረት፣ ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ዕድገት መጠን እና ለውጭ ገበያ የሚውሉ ምርቶችን ለማምረት የሚያስችል የእርሻ መሬት ፍላጎት የቆላ ደን መሬቶች ወደ እርሻ መሬትነትና የመኖሪያ አካባቢነት ለመቀየራቸው አብይ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የቆላ ደን አካባቢዎች በአገሪቱ ከፍተኛ የደን መውደም እየደረሰባቸው ካሉ ስፍራዎች ዋናዎቹ ናቸው፡፡



የዕጣን ምርት ምንጭ የሆነው የዕጣን ዛፍ (*Boswellia papyrifera*) በቆላ ደን ውስጥ ከሚገኙ ጠቃሚ የዛፍ ዝርያዎች መካከል አንዱ ነው።

© A. Eshete

**የቆላ ደን ለቤተሠብና ለአገር ኢኮኖሚ ያለው ድርሻ አነስተኛ እንደሆነ ተደርጎ ይታሰባል።** በእርግጥ የቆላ ደን የደጋ ደንን ያህል ለምለምና ጥቅጥቅ ያለ አይደለም። የምርት ውጤቶቹም የገበያ ዋጋ አነስተኛ ሲሆን ከሌሎች የደን ውጤቶች ያነሰ ጥራት ያላቸውና ለመደበኛ ስራ ፈጠራና ኢኮኖሚ ያላቸው አበርክቶት ውስን ነው። በዚህ ሳቢያ የቆላ ደን መሬቶች የተሻለ የኢኮኖሚ አዋጭነት አላቸው ተብለው ወደሚታሰቡ የመሬት አጠቃቀሞች እንዲቀየሩ ሲደረግ ይስተዋላል። ነገር ግን እንደ እርሻ ከመሳሰሉ የመሬት አጠቃቀሞች ጋር ሲነፃፀር የቆላ ደን የሚሰጠው ምርትና ግልጋሎት እንዲሁም በአካባቢው ያሉ ባለድርሻ አካላት ደኑን ለመንከባከብ የሚያወጡት ወጪ በሚገባ የተመዘገበና የታወቀ አይደለም። በተጨማሪም አብዛኛዎቹ የእንክብካቤ ወጪዎች የገበያ ዋጋቸው ግልጽ ካለመሆኑ በላይ ጥቅማቸው በረጂም ጊዜ የሚታይ ናቸው።

**ይሁን እንጂ ይህን በፖሊሲ አውጪዎችና በማኅበረሰቡ በተገቢ ሁኔታ ግንዛቤ ያልተወሰደበትን የቆላ ደን በዘላቂ ሁኔታ መንከባከብና መጠበቅ እንዳለብን የሚመለክቱ ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ምክንያቶች አሉ።** ኢትዮጵያ የእንጨት ውጤቶችን ጨምሮ አብዛኛውን የኢንዱስትሪ ምርቶች ከውጭ ታስገባለች። ይህም የውጭ ምንዛሬ እጥረት ከማባባሱ በላይ አገሪቱ የውጭ ምንዛሬ በሚያስገኙ ምርቶች ላይ እንድታተኩር አስገድዷታል። በሌላ በኩል አገሪቱ ከቆላ ደን በገፍ የሚገኙ ማር፣ ዕጣን፣ ሙጫ እና ጥሬ ቀርከሀ የመሳሰሉ የደን ምርቶችን ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ታገኛለች። በተጨማሪም የቆላ ደን የኤሌክትሪክ ኃይል ለሚያመነጩት የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድቦች የውኃ ምንጭ የሆኑትን ተፋሰሶች ከመጠበቁ በላይ በቅርብና በርቀት ለሚኖሩ ሰዎች (የስደተኛ ካምፖችን ጨምሮ) ዋና የማገዶ እንጨትና ከሠል ምንጮችም ናቸው።



© A. Eshete

የቆላ ደን ለቤት እንስሳት የግጦሽ ምንጭም ነው።

**ማንኛውም የመሬት አጠቃቀም ውሳኔ የቆላ ደን ለሌሎች ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች የሚሰጠውን ጠቀሜታ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል።** እንዲሁም ደኑ በርቀት ላሉ ማኅበረሰቦች የሚሰጠውን ጠቀሜታ ከሌሎች አካባቢ በማምጣት ለማቅረብ ቢሞከር የሚወጣውን የማጓጓዣ ወጪና የአካባቢው ሕብረተሰብና ግለሠቦች የደን ኃብቱን ለመንከባከብና ለመጠበቅ የሚያወጡትን ወጪ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይገባዋል። የቆላ ደን ለገጠሩ ሕብረተሠብ ዕጅግ ጠቃሚ የሆኑ የተለያዩ የዱር አራዊት፣ ዕፅዋት፣ ሳርና የተለያዩ ጠቃሚ ቅጠላ ቅጠሎች መኖሪያና መገኛ ነው። በቆላ ደኖች ውስጥ የሚገኘው ብዝኃ-ሕይወትም አገሪቱን በዘርፉ ከመሪ አገራት ተርታ እንድትሰለፍ አስችሏታል። በተጨማሪም የቆላ ደን ለሌሎች ክፍለ-ኢኮኖሚዎች ግብዓትና ለሕብረተሠቡ ዘላቂ ህይወት ዋስትና ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ግልጋሎቶችና ስነ-ምሕዳራዊ ጠቀሜታ ያበረክታል። የውኃ ምንጮችን መጠበቅ፣ የአፈር መሸርሸርን መከላከል፣ የበረሀነት መስፋፋትን ለመከላከል ከለላ መሆን እና የማገዶ እንጨት፣ የከሠል፣ የከብት መኖ፣ የባህላዊ መድኃኒት፣ የአደን ስጋ፣ የግንባታ ግብዓትና በድርቅ ወቅቶች ለምግብነት የሚውሉ ስራ ስርና ቅጠላ ቅጠል ምንጭነት ከቆላ ደን ስነ-ምሕዳራዊ ጠቀሜታዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ለምሳሌ በቀላሉ ተደራሽ ባልሆኑ አካባቢዎች ድርቅ በሚከሰትበት ወቅት የከብቶች መኖ በአካባቢው ከሚገኝ የቆላ ደን ማዘጋጀት መኖውን ከሌላ ስፍራ አጓጉዞ ከማቅረብ ጋር ያለው ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት በሚገባ ግንዛቤ አልተወሰደበትም። ከሕግ አንፃር በኢትዮጵያ ሁሉም የቆላ ደኖች በመንግስት ባለቤትነት ስር ናቸው። በተግባር ግን እነዚህ ደኖች የሚንከባከቧቸውና የሚጠቀሙባቸው በየአካባቢው የሚገኙ ሕብረተሠብና ግለሠቦች ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህን ደኖች ለመንከባከብና ለመጠበቅ ሕብረተሠቡና ግለሠቦቹ ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውንና ጉልበታቸውን ቢያወጡም፤ በደኖቹ ላይ ያላቸውን የተጠቃሚነት መብት በግልጽ የሚያሳይ ስርዓት የለም። በመሆኑም ደኑን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ሲተላለፉ እነዚህ ለእንክብካቤ የሚወጡ በገንዘብ ተሰልተው ግምት ውስጥ የሚገቡበት አሰራር ገና አልተዘረጋም።

**ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ መንግስት የቆላ ደንን ጨምሮ በሁሉም ዓይነት ደኖች ላይ ዘላቂ የደን አስተዳደር ሥርዓት ማስፈን ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ይገኛል።** የደን ጉዳይ በቁልፍ የአገሪቱ የፖሊሲ፣ ሕግና አፈጻጸም ዶክመንቶች ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶት ተካትቷል። «ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ»፣ «ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ፕላን»፣ እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ አገራዊ የካርቦን ልቀት ቅነሳ አገራዊ ድርሻ ዕቅድ[1]» ከነዚህ ቁልፍ ዶክመንቶች ውስጥ ይካተታሉ። እ.ኤ.አ በ2013 የአካባቢ ጥበቃ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር እንዲቋቋም ተደርጓል። ኢትዮጵያ የደን ካርቦን ልቀት ቅነሳ ፕሮግራም (REDD+) ከሚተገብሩ የአፍሪካ አገራት በግምባር ቀደምትነት ትገኛለች። በዚህም ደኖቹ ከአየር ውስጥ መጥጠው የሚያስወግዱትን በካይ አየር መጠን የመለካት ሒደት ውስጥ የክትትል፣ የማረጋገጥና የሪፖርት ስርዓትም (Monitoring, Reporting and Verification (MRV)) በአገርና በክልል ደረጃ ተዘርግቷል። ከዚህ በላይ እ.ኤ.አ በ2018 አዲስ የደን ሕግ ታውጇል። አዲሱ አዋጅ ቀደም ሲል የነበረውን በደን ጥበቃ ላይ ያተኮረ አመለካከትና አሠራር በመቀየር ሕብረተሠቡና ሌሎች አያሌ ባለድርሻ አካላት ጥቅም ሊያገኙበት በሚችሉበት ዘላቂ የደን እንክብካቤና አስተዳደር ላይ ትኩረቱን አደርጓል።

1 the Nationally Determined Contribution (NDC) in mitigating and adapting to climate change submitted to the United Nations Framework Convention on Climate Change (UNFCCC)



ሴቶች ከቆላ ደን የተሠበረ የማገዶ እንጨት ሲገበያዩ፤ አሶሳ ገበያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል።

**ይህ ዶክመንት ስለ ዘላቂ የቆላ ደን አገራዊ ሁኔታ መረጃ በመስጠት ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የቆላ ደን ዘላቂ አስተዳደርና እንክብካቤ ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ውስጥ የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል የሚል እምነት አለን።** የዶክመንቱ ዋና ዓላማ ውሳኔ ሰጪ አካላት ስለ ቆላ ደን ያላቸውን የግንዛቤ ክፍተት በመሙላት የኃብቱን ትክክለኛ ዋጋ እንዲረዱ ለማስቻል የታለመ ጭምር ነው። በኢትዮጵያ የቆላ ደንን የሚመለከቱ ጥናቶች በተበታተነ ሁኔታ በተወሰነ አካባቢና በተወሰኑ የደኑ ኃብቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ይህ ዶክመንት በእነዚህ የተበታተኑ የታተሙና ያልታተሙ ጥናቶች ላይ በመመርኮዝ እንዲሁም በፌዴራልና በክልል ደረጃ ያሉ ቁልፍ መረጃ ሠጪዎች ጋር ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና በአሶሳና አዲስ አበባ ሁለት ወርክሾችን በማካሄድ የተገኙ መረጃዎችን በማጣመር የአገሪቱን የቆላ ደን ኃብት ሁኔታ ይተነትናል።።

ዶክመንቱ የአለም የእርሻና ምግብ ድርጅት «ከሠሀራ በታች ባሉ አገራት ቆላማ አካባቢዎች ዘላቂ የደን አስተዳደር ለመተግበር የሚያስችል መመሪያ» በሚል ባወጣው ዶክመንት ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ ነው። ጥናቱ የተ.መ.ድ-ሬድ (UN-REDD) በአለም የእርሻና ምግብ ድርጅት የቴክኒክ ድጋፍ ፕሮግራም በኩል ባደረገው የገንዘብ ድጋፍ በአለም የደን ምርምር ማዕከል (Center for International Forestry Research-CIFOR) እና በአካባቢ ጥበቃ፣ ደንና የአየር ለውጥ ሚኒስቴር በትብብር የተካሄደ ነው።

የፊት ለፊት ሽፋን፦ በክረምት ወራት አረንጓዴ ለብሶ የሚታይ በአባሎ ዛፍ የተመላ የቆላ ደን፤ መተማ፤ አማራ ክልላዊ መንግስት፤ ኢትዮጵያ። ፎቶ በአበጀ እሸቴ።

ይህ የሕትመት ውጤት በዴንማርክ፣ ጃፓን፣ ሉክሰምበርግ፣ ኖርዌይ፣ ስፔን፣ ስዊዘርላንድ መንግስታት እና በአውሮፓ ሕብረት ድጋፍ የታተመ ነው።

**fao.org | cifor.org | forestsnews.cifor.org**

**Food and Agriculture Organization of the United Nations**

የአለም የእርሻና ምግብ ድርጅት (FAO) ረሀብን ለማጥፋት የሚደረገውን አለም አቀፍ ጥረት የሚያስተባብር በተ.መ.ድ ስር የተቋቋመ ድርጅት ነው። ድርጅቱ ሰዎች ሁሉ የተረጋገጠ የምግብ ዋስትና ኖሯቸው በቂና የተመጣጠ ምግብ ሁልጊዜም በማግኘት ጤናማ ሕይወት እንዲኖሩ ማስቻልን ዋና ዓላማው አድርጎ ይንቀሳቀሳል። ከ194 አገሮች በላይ በአባልነት በማቀፍና ዋና ጽ/ቤቱን ሮም (ጣልያን) ውስጥ በማድረግ፤ የአለም የእርሻና ምግብ ድርጅት ከ130 በላይ በሆኑ አገሮች ውስጥ ስራውን ያከናውናል።

**CGIAR — RESEARCH PROGRAM ON Forests, Trees and Agroforestry**

CGIAR የሚያካሂደው የደን የዛፎችእና የጥምር እርሻና-ደን ጥናት በአለም ትልቁ የልማት ምርምር መርኃ-ግብር ሲሆን ለዘላቂ ልማት እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥን ለመቅረፍ የደን የዛፎች እና የጥምር እርሻና-ደንን ሚና ለማሳደግ ያለመ ነው። የዓለም አቀፉ የደን ምርምር ማዕከል (CIFOR) ከCATIE፣ CIRAD፣ ICRAF፣ INBAR እና TBI ጋር በመተባበር FTAን ይመራል። የCIFOR ተግባራት በአለም አቀፍ የግብርና ምርምር አማካሪ ቡድን ፈንድ (CGIAR Trust Fund) ድጋፍ ይካሄዳሉ። cgiar.org/funders

**CIFOR**

**የዓለም አቀፉ የደን ልማት ጥናት ማዕከል (CIFOR)**
የዓለም አቀፉ የደን ልማት ጥናት ማዕከል (CIFOR) ለዋጭ (አዳዲስ) ምርምሮችን በማከናወን የልማት አጋሮችን አቅም በማጎልበትና በደን እና በሰዎች ላይ ተፅዕኖ ያላቸውን ፖሊሲዎች እና አሰራሮች በማስታወቅ የሰዎች ደህንነት፣ ፍትሃዊነትና እና አካባቢያዊ ደህንነት እንዲጠበቅ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት ይሰራል። CIFOR ከCGIAR የምርምር ማዕከላት አንዱ ሲሆን የደን የዛፎችእና የጥምር እርሻና-ደን (FTA) ጥናት መርሃግብሩን ይመራል። ዋና መስሪያ ቤቱም ቦጎር ኢንዶኔዥያ ሆኖ በኬንያ ናይሮቢ፣ በካሜሩን ያዉንዲ ፣ በፔሩ ሊማ እና በቦን ጀርመን ቢሮዎች አሉት።

Some rights reserved. This work is available under a CC BY-NC-SA 3.0 IGO licence

© FAO, 2019
CA3752AM/1/03.19